# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው።

**EHRCO** stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

## በተያዙ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው ሰቆቃ ይቁም!

## 99ኛ ልዩ መግለጫ

መጋቢት 21 ቀን 1999 ዓ.ም

ኢትዮጵያ የተቀበለችው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ማንም ሰው ላይ ጭካኔ የተሞላበት ኢሰብአዊ ወይም ክብርን በሚያዋርድ አያያዝ መያዝ አይገባውም፤ በዚህ ሁኔታም አይቀጣም ይላል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 7 ላይ ይህንኑን መብት ያረጋግጥና ይህ መብት በማናቸውም ሁኔታ የማይገሰስ መሆኑን በአንቀጽ 4(2) ሥር ይደነግጋል። የኢፌዴሪ ህገ-መንግስትም በአንቀጽ18(1) ሥር ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ የመጠበቅ መብት እነዳለው ይደነግጋል። በተጨማሪም አንቀጽ 15 ማንም ሰው በህግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ህይወቱን እንደማያጣ ሲደነግግ እነዚህ መብቶች የማይደፈሩና የማይገሰሱ መሆናቸውንም አንቀጽ 14 ያረጋግጣል።

ይሁን እንጂ ይህንን ህገ-መንግስታዊና የዓለም አቀፍ ሥምምነት ድንጋጌ በመተላለፍ በአቶ ፀጋዬ አየለ ይግዛው ላይ ማሰቃየትና ድብደባ ከተፈጸመባቸው በኋላ በእስር ላይ ሆነው ህክምና በመከታተል ላይ እያሉ ህይወታቸው አልፏል።

ፀጋዬ አየለ ይግዛው በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚኖሩ ባለትዳር እና የሶስት ቤተሰብ አባላት አስተዳዳሪ፣ የኢዴፓ አባል፣ የ34 አመት ጎልማሳና በጎንደር ሆስፒታል የራዲዮሎጂ ባለሙያ እንደነበሩና ከዚያም በጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም ፖሊሶች ሊይዟቸው ሲከታተሏቸው ወደ ደብረማርቆስ ከተማ መጥተው በግል ክሊኒክ በራዲዮሎጂ ሙያ ተቀጥረው ያገለግሉ ነበር። ታህሳስ 9 ቀን 1999 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 2፡45 ሰአት ወደሚሰሩበት መስሪያ ቤት በመግባት ላይ እንዳሉ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በፖሊስ ተይዘው ደብረማርቆስ እና ባህር ዳር ከተማ ለስምንት ቀናት ከታስሩ በኋላ ታህሳስ 17 ቀን 1999 ዓ ም ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል መከላከልና ምርመራ መምሪያ አንዲመጡ ተደርጎ ከታሰሩ በኋላ «የአርበኞች ግንባር አባል ነህ? እከሌን ታውቃለህ ወይ?» እየተባሉ እየተጠየቁ በተለያየ ጊዜያት ምርመራ ቢሮ ውስጥ ለብቻ ታስረው በአሰቃቂ ሁኔታ እንደተደበደቡ በቤተሰብ አማካኝነት ካሉበት እስር ቤት አቤቱታቸውን ማንነታቸውን በሚገልጽ ፎቶግራፍ በማስደገፍ የካቲት 21 ቀን 1999 ዓ.ም በጽሑፍ ለኢሰመጉ አመልክተዋል። በተለይም ከጥር 2 እስከ ጥር 11 ቀን 1999 ያለ እህል ውሀ በጣም ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ እጅና እግራቸውን በካቴና ታስረው አውጣ እየተባሉ በጣውላ ጀርባቸው እና መቀመጫቸውን እንደተመቱ፣ ሰውነታቸው ሲዝልም ወለል ላይ ጥለዋቸው እንደሚሄዱ እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወደ ራስ ደሰታ ሆስፒታል

ተወስደው ለ16 ሰአት እራሳቸውን ሳያውቁ ቆይተው በተደረገላቸው ህክምና ህይወታቸው ነፍስ እንደዘራና ወዲያውኑም ወደ አዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ እንዲመለሱ ተደርጎ "ካሁን በፊት የለፈለፍከውን ተናገር" እየተባሉ በቪዲዮ ካሜራ መቀረፃቸውንና በተፈፀመባቸውም ድብደባ ምክንያት፦

- የሁለት እጆቻቸው ክንዳቸው ስሜት እንደሌላቸው፣
- ግራ ጆሮአቸው በጥፊ እና በቦክስ ከመመታቱ የተነሳ የመስማት ችግር እንደገጠማቸው፣
- የግራ እግር ጥፍራቸው መነቀሉን፣
- አይናቸው የፀሐይ ብርሃን በሚያዩበት ጊዜ ብዥ የማለት እና የአእምሮ መረበሽ ችግር እንዳጋጠማቸው ገልጸዋል።

እንዲሁም በወቅቱ በተመሳሳይ ሁኔታ አብረው ታስረው የነበሩ ግለሰቦችም ከእስር ከተፈቱ በኋላ ሟች በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜ አካላቸው ላይ የደረሰውን የጉዳት ሲገልጹ ቀኝ እጃቸውና እግራቸው በእግር ብረት እንደታሰረ ምልክት እንደሚታይና ለመንቀሳቀስ እንደሚሳነው፣ ጆሮአቸው እንደማይሰማ እና መላ አካላቸው ላይ የቀጥቀጥ ምልክት እንደሚታይበትና ሟችም በህይወት እያሉ ጉዳት እንደደረሰባቸው የነገሯቸው መሆኑንና በድብደባው ምክንያት ጤንነታቸው ተቃውሶ ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉ መሆኑን አረጋግጠዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጊዜ ቀጠሮ ወቅት ፖሊስ ከሰባት ጊዜ ላላነሰ «ምርመራ አላጠናቀቅኩም» በማለት ፍ/ቤቱን የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆ ጉዳዩ በተደጋጋሚ ከተቀጠረ በኋላ ፍ/ቤቱም በመጨረሻ የካቲት 26 ቀን 1999 ዓ.ም ቀጠሮ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ አልሰጥም በማለት መዝገቡን ዘግቷል። ነገር ግን ታሳሪው በምን ሁኔታ መቆየት እንዳለባቸው የሰጠው ትእዛዝ ባለመኖሩ አዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ መምሪያ በእስር ላይ ቆይተው ቤተሰብ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 9ኛ የፍ/ብሄር ችሎት የአካል ነፃ ማውጣት ክስ መስርቶ መጋቢት 17 ቀን 1999 ዓ.ም ፋይላቸው ከሌሎች ተመሳሳይ ተከሳሾች ጋር ቀርቦ ከዕስር እነዲፈቱ ፍ/ቤቱ ቢወስንም በዚሁ ዕለት በራስ ደስታ ሆስፒታል በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሆነው በህክምና ላይ እንዳሉ ከውሳኔው ጥቂት ቀደም ብሎ በግምት ከቀኑ 4:30 ሰአት ህይወታቸው አልፏል።

በ17/7/1999 አስከሬናቸው በፖሊስ አማካኝነት ለምርመራ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተልኮ ሆስፒታሉም አስከሬኑ የተመረመረ መሆኑን የሚገልጽ «ለሚመለከተው ሁሉ» የሚል በ18/7/1999 የተጻፈ ደብዳቤ ገንዘብ ከከፈሉበት ደረሰኝ ጋር ለቤተሰብ ተሰጠ ሲሆን የምርመራው ውጤት ግን ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ድረስ ለቤተሰባቸው እንዳለተሰጠ ኢሰመጉ በስፍራው ተገኝቶ ያረጋገጠ ሲሆን በዚሁ ዕለት ቤተሰብም አስከሬናቸውን ተረክቦ ወደ ተወለዱበት ስፍራ ወደ ደብረማርቆስ ከተማ በመሄድ የቀብር ሥነ-ስርዓታቸው በ19/7/1999 ተፈጽሟል።

## ማጠቃለያ

ኢሰመጉ ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለጸውን ጉዳይ ሟች በህይወት እያሉ ከእስር ቤት ሆነው ድብደባ የደረሰባቸው መሆኑን በቤተሰቦቻቸው አማካኝነት የገለጹበትን አቤቱታ፣ አብረው ታስረው የነበሩትን የምስክሮች ቃል በመቀበል እንዲሁም አስከሬናቸው

*ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል እንዲሄድ ተደርጎ ምርመራ ተደርጎለት ቤተሰብ እስከሚረከብ ድረስ ያለውን ሁኔታ ተከታትሎ ለማረጋገጥ ችሏል።*

*በመሆኑም መንግሥት*

- *የግለሰቡን የአሟሟት ሁኔታ በተገቢው መንገድ እንዲጣራ አድርጎ የድርጊቱን ፈፃሚዎች ለፍርድ እንዲያቀርብ፣*
- *የአስከሬን ምርመራ ውጤቱንም ለቤተሰባቸው እንዲያሳውቅ፣ እና*
- *በእስረኞች ላይ የሚፈጸመው ኢሰብዓዊ ድርጊትም በአስቸኳይ እንዲቆም እነዲያደርግ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።*

*በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግስት በአገሪቱ ህገ-መንግስት የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶች እንዲያከብርና እንዲያስከብር በሚከተሉት አድራሻዎች በመፃፍና በመደወል የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል።*

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-1) 155 0900***
  **ስልክ (251-1) 1241013**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-1) 155 0722***
  **ስልክ (251-1) 124 2301**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኘሬዚዳንት**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-1) 155 2020***
  **ስልክ (251-1) 551 8850**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-1) 155 2020***
  **ስልክ (251-1) 122 6767**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈርጌሣ**
  **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር**
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-1) 552 0000***
  **ስልክ (251-1) 552 0000**
  **አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

- ***ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ***
  ***የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስትር***
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-1) 552 0874***
  ***ስልክ (251-1) 551 5099***
  ***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***

- ***ክብርት ዶ/ር ምሥራቅ መኮንን***
  ***የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ***
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 312፣ ፋክስ (251-1) 058 220 1068***
  ***ስልክ (251-1) 058 220 2252***
  ***ባሕር ዳር፣ ኢትዮጵያ***

- ***ክቡር ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበዬሁ***
  ***የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር***
  ***ፖ. ሣ. ቁጥር 199፣ ፋክስ (251-1) 153 4253***
  ***ስልክ (251-1) 551 2744***
  ***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***

- ***ክቡር ኮሚሽነር በፈቃዱ ሰቦቃ***
  ***የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር***
  ***ፖ. ሣ. ቁጥር 5647፣ ፋክስ (251-1) 155 0360***
  ***ስልክ (251-1) 156 0115***
  ***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***

- ***ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት***
  ***የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር***
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-1) 645 9290***
  ***ስልክ (251-1) 645 9228***
  ***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***

- ***ክቡር አቶ አባይ ተክሌ***
  ***የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ዋና እምባ ጠባቂ***
  ***ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-1) 645 9229***
  ***ስልክ (251-1) 663 5090 663 5363***
  ***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***